# የኢትዮጵያንና የሱዳንን የድንበር ጉዳይ አስመልክቶ ከዓለምአቀፍ የትግራይ ተወላጆች ሕብረት ለፍትሕና ለዲሞክራሲ የተሰጠ የአቋም መግለጫ

የኢትዮጵያና የሱዳን ሕዝብ በወንድማማችነት ላይ በተመሰረተ የመከባበርና የመተጋገዝ የረዥም ዓመታት ግንኙነት ያለው ሕዝብ በመሆኑ፤ ሁለቱም ሕዝቦች በተለያዩ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ሁኔታዎች እዲሁም በድርቅና ረሃብ አስገዳጅነት በተለያዩ ወቅቶች በየአገሮቻቸው በተፈጠሩ አደገኛ ሁታዎች ሲፈናቀሉ አንዱ ወደ አንዱ እየተሰደደ እንደሁለተኛ ቤቱ የሚጠለልበት ብሎም የሚኖርበት ሁለተኛ አገሩ መሆኑ ይታወቃል።

የሁለቱ መንግስታትና ሕዝቦች ግንኙነት መሰረቱ የፀናና ለአፍሪካ ቀንድ አርኣያነቱ የጎላ ቢሆንም፤ የእንግሊዝ ቅኝ ገዥዎች ከረዥም ዓመታት በፊት ባልተሟላ መልኩ የከለሉት የሁለቱ አገሮች አዋሳኝ ድንበር ግን በየወቅቱ ታሪካዊ የድንበር ላይ አለመግባባቶች እየተከሰቱበት፣ መንግስታዊ ግንኙነቶችና ውይይቶች እየተካሄደበት፣ ከዚያም አልፎ በሁለቱ አገሮች የድንበር አካባቢ ነዋሪ ሕዝቦች መካከል የንብረትና የሰው ህይወት የተገበረበት ግጭቶችንም እያስከተለ፤ ረዘም ያሉ ዓመታትና በርካታ መንግስታት እንዳለፉበት ሆኖም ግን እስከ ዛሬ ዘለቄታዊ እልባት እንዳላገኘ የሚታወቅ ነው።

ካለፉት ወራት ጀምሮ ከአገር ውጭ በተለይም በዋሽንግተን ዲሲ እና አካባቢው በሚገኙ የሕዝብ መገናኛ አውታሮች በኩል፤ "...የኢትዮጵያ መንግስት ሰፊና ለም የአገራችንን መሬት ለሱዳን አሳልፎ ሰጠ..." የሚል ሰፊ ስርጭት እየተካሄደ ይገኛል። በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ መንግስት ተወካዮች፤ "... ሐሰት ነው፤ አንድም ቅንጣት መሬት የተሰጠ የለም፤ ነገር ግን በሁለቱ አገራት መካከል ለረዥም ዓመታት ሲንከባለል ወደዚህ ትውልድ የተላለፈውን የአገራቱን የድንበር ጉዳይ ለዘለቄታው ለማካለል እንዲያስችል ሶስት ዓመታት ዕድሜ ያስቆጠረ የጋራ ኮሚሽን አቋቁመን አብረን እየሰራን ነው..." ሲሉ ይሰማል።

የኢትዮጵያ መንግስት የሚለው ነው እውነት ወይንስ ከአገር ውጭ በተለይም በዋሽንግተን አካባቢ በስፋት እየተሰራጨ ያለው መሬት ከድንበራችን ተቆርሶ ለሱዳን የመሰጠቱ ዜና? ለዚህ ጉዳይ መልስ ለመስጠት የሚያስችል በቂ ማስረጃ ባይኖረንም፤ አነሳሳችን፤ እንደማንኛውም ለአገሩና ለሕዝቡ ቀናዒ የሆነ ዜጋ አገራችንንና ሕዝባችንን የሚነኩ ጉዳዮች ሁሉ ስለሚያሳስቡን፤ ከዚህም ከዚያም በስፋት እየተነገረለት ባለው በዚህ የኢትዮጵያና የሱዳን የድንበር ጉዳይ ላይ አቋማችንን ለመግለፅ ነው።

የተለያዩ ታሪካዊ ሰብአዊና ሰነዳዊ ማስረጃዎች እንደሚያስረዱት፤ የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር በተለይም የአማራና የትግራይ ክልሎችን ከሱዳን በሚያዋስነው ድንበር ላይ ረዘም ያሉ ዓመታትንና የተለያዩ የሁለቱን አገራት መንግስታት ያሳለፈ የመሬት ይገባኛል ውዝግብና፣ የመንግስታቱን ቀጥተኛ ግንኙነቶችን የጠየቁ በርካታ የጋራ ኮሚቴዎች መቋቋምና ተከታታይ ጥናቶችና ውይይቶች መካሄዳቸው የሚታወቅ ነው:: በተለይም ከዓፄ ሃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ በደርግ መንግስትም የቀጠለ፤ ነገር ግን መቋጫ እልባት ያልተበጀለት እስከ አሁን በእንጥልጥል የሚገኝ የድንበር አከላለል መኖሩ በሁሉም ወገኖች ዘንድ የሚታወቅ ታሪካዊ ሂደት ነው::

አሁን በሁለቱም አገራት በስልጣን ላይ ያሉት መንግስታት ይህን ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተንከባለለ ለዚህ ትውልድ የተረፈው የድንበር ላይ ውዝግብ የመጨረሻ መቋጫ እልባት እንዲያገኝና የሁለቱም አገራት አዋሳኝ ድንበር በአግባቡ እንዲከለል የማድረግ ታሪካዊ ሃላፊነት ስላለባቸው፤ የጋራ ኮሚሽን አቋቁመው ለመፍትሄው መንቀሳቀሳቸው ተገቢ መሆኑን ብናምንበትም፤ በሚከተሉት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ግን የአገራችን መንግስት ምን ያህል ጥንቃቄ እንዳደረገ በቂ መረጃ ስላላገኘን ስጋት እንደተሰማን ለመግለፅ እንወዳለን::

አንደኛ፤ የጋራ ድንበር ጉዳይ ባለቤትና ጉዳዩ በዋነኛነት የሚመለከተው ብሎም አካላይ ቦታዎችንና ምልክቶችን በማወቅ ዋነኛ መረጃ የድንበር አካባቢ ነዋሪ ሕዝብና የአገር ሽማግሌዎች፤ እንዲሁም ቀደም ባሉት መንግስታት የተካሄዱ ጥናቶችና የጋራ ውይይቶች ውጤት የሆኑ ሰነዳዊ ማስረጃዎች፣ በእነዚህ ሂደቶች ውስጥ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተካፋይ የነበሩ በሕይወት የሚገኙ ሰብዓዊ ማስረጃዎች በመሆናቸው፤ መንግስት የሕዝብ ወኪል እንደመሆኑ ከወቅቱ የሱዳን መንግስት ጋር ለሶስት ዓመታት የዘለቀ የጋራ ኮሚሽን አቋቁሜ ለድንበር መካለል እየሰራሁ ነኝ ሲል እነዚህን ዋነኛ ማስረጃዎችና መረማመጃ መሰረቶች በምን መልኩ ተጠቅሞባቸዋል? ይህም ጉዳይ በምን መልኩ በግልፅነትና ተዓማኒነት እየተከናወነ ስለመሆኑ አሳስቦናል::

ሁለተኛ፤ ከዚህ የድንበር ውዝግብ ጋር በተያያዘ ዜጎቻችን ከመኖሪያ ቀያቸው በሱዳን ወታደሮች ታፍነው እንደተወሰዱና በሱዳን መንግስት እስርቤት ታጉረው እንደሚገኙ በዋሽንግተን አካባቢ ከሚሰራጩት የመረጃ አውታሮች ብቻም ሳይሆን በዋሽንግተን የኢትዮጵያ ኤምባሲ ተወካይም "አገር ፍቅር" ተብሎ በሚታወቀው የሬዲዮ ስርጭት ቀርበው ያረጋገጡት ሐቅ ነው:: ይህም የሱዳን ወታደሮችና መንግስት ተግባር የአገራችንን ሉዓላዊ ድንበርና የዜጎቻችንን መብት የጣሰ የወረራ ተግባር እንደመሆኑ፤ የአገራችን መንግስት እንዴት በዝምታና በቸልተኝነት እንዳለፈው፣ እንዴትስ ለሕዝብና ለአገራችን ፓርላማ ግልፅ እንዳልተደረገ፣ እንዴትስ የዜጎቻችንን መብት ለማስከበር ተገቢው ሕጋዊና ዲፕሎማሲያዊ እርምጃ እንዳልተወሰደ፤ ግልፅ ሊሆንልን አልቻለም:: በዚህ

በአገርና በሕዝብ ላይ በተፈፀመ ሕገወጥና የአገርን ክብርና ሉዓላዊነት በሚነካ ተግባርም በመንግስት ግልፅነትና ተአማኒነት ላይ ይበልጥ እንድናስብበት አድርጎናል::

የኢትዮጵያ መንግስት የአገራችንንና የሕዝባችንን ታሪክና እሴቶች፣ ክብርና ሉዓላዊነት፣ ሕግና ሕገመንግስት፣ ከግለሰብ መብት አንስቶ የዜጎችን መብትና ጥቅም፣ ወዘተ... የመጠበቅና የማስጠበቅ ሃላፊነት አለበት ብቻም ሳይሆን፤ በግልፅነትና በተጠያቂነት የወከለውን ሕዝብና የሚያስተዳድረውን አገር ማገልገል እንዳለበት የአገራችን ሕገመንግስት የደነገገውና የዜግነትም ግዴታው ነው:: ታሪካችን የነፃነት ታሪክ፣ የራሳችንን የማንሰጥና የእኛ ያልሆነውንም የማንመኝ የማንፈልግ፣ የአገራችንን ድንበር ሆነ ማንነታችንን በሃይል ለመንካት ለሚከጅሉት ግን ምሕረት እንደሌለን፣ ወዳጆቻችንን አክባሪዎችና እንግዳ ተቀባዮች መሆናችንን፤ ወዳጆቻችንም ሆኑ ጠላቶቻችን ጠንቅቀው የሚያውቁት የማንነታችን መገለጫ ሐቅ ነው::

ዛሬ በስልጣን ላይ ያለው መንግስትም ይህን ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወራረስ የመጣ የሚያኮራ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ የሆነ እሴት ጠብቆና አስጠብቆ፤ የኢትዮጵያና የሱዳን የድንበር ጉዳይ የመጨረሻ እልባት የሚያገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸቱ ላይም ሆነ በሌሎች አገርንና ሕዝብን በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ውይይቶችና ስምምነቶች ሂደት ውስጥ ሁሉ፤ ዋነኛው ባለጉዳይ ሕዝባችን በአግባቡ መሳተፍ እንዳለበት ሂደቱና አፈፃፀሙም ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለው አኳኋን እንዲተገበር ስንል በዜግነታችን አጥብቀን እንጠይቃለን::

የትግራይ ተወላጆች ዓለምአቀፍ ሕብረት ለፍትሕና ለዲሞክራሲ
ግንቦት 23 ቀን 2000 ዓ/ም
ዋሽንግተን ዲሲ